207


በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን


# *የ1995 በጀት ዓመት*

# *የስታቲስቲክስ ሥራ ዕቅድ*


አዲስ አበባ

ሚያዝያ 1994

5

# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# *የ1995 በጀት ዓመት*

# *የስታቲስቲክስ ሥራ ዕቅድ*


አዲስ አበባ

ሚያዝያ 1994

# ማውጫ

**አርዕስት** **ገጽ**


1. መግቢያ ........................................ 1

2. የ1994 የስምንት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ........................ 2

3. የ1995 የሚካሄድ ጥናት የዕቅድ ዓላ፡ማዎች የአፈጻጸም ስልቶች ......... 7

4. የ1995 ዕቅድ ይዘት ........................................ 8

5. የ1995 ካፒታል በጀት ፍላጎትና መግለጫ ................................ 9

6. የ1995 የካፒታል በጀት ፍላጎት በወጪ ዓይነት ........................ 12

7. የ1995 ጥናቶች ግብና መግለጫ ........................................ 22

8. የ1995 የሰው ኃይል ፍላጎት ........................................ 31

9. የ1995 ጥናቶች መርሀ-ግብር ........................................ 32

10. የ1995 የካፒታል በጀት መጠየቂያ ቅጽ ................................ 41

11. ትኩረትና መመሪያ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ............................ 48

# የ1995 የስታቲስቲክስ ሥራ ዕቅድ

## 1. መግቢያ

መንግሥት ለሚወጥናቸው ዕቅዶችና ለሚያዘጋጃቸው ፕሮግራሞች በየዘርፉ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ሊገልጽ የሚችል ወቅታዊ፣ የተሟላና አስተማማኝ የሆነ ስታቲስቲካዊ መረጃ መኖር ወሣኝነት አለው:: በተጨማሪም እነዚህ መረጃዎች የታቀዱ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች በተግባር ላይ ሲውሉ ለመከታተልና ግምገማ ለማካሄድም ጠቃሚነታቸው የጎላ ሲሆን፣ በተለያዩ የኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ መስኮች ዙሪያ ለሚካሄዱ ጥናቶችና ምርምሮችም ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል::

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የአገሪቱን የስታቲስቲክስ መረጃ ፍላጎት በማሟላት ረገድ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣትና ለብሔራዊ ስታቲስቲክስ መረጃ ዕድገት አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በየጊዜው የተሻሻለ የአሠራር ዘዴዎች ላይ በመመርኮዝ የመንግሥትን የመረጃ ፍላጎትን ከፍተት ለማሟላት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፣ አሁንም በማካሄድ ላይ ይገኛል:: መ/ቤቱ ለዓላማው መሣካትም የተለያዩ ጥናቶችን በማካሄድና መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማቀነባበርና በመተንተን ሪፖርቶችን እያዘጋጀ ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት ላይ ይገኛል::

የባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንግሥትን የልማት የትኩረት አቅጣጫና የመረጃ ፍላጎትን ግምት ውስጥ በማስገባት እንደዚሁም የመ/ቤቱን የማስፈፀም አቅም በመገምገም በ1995 በጀት ዓመት ቅድሚያ ተሰጥቶአቸው ቢጠኑ ያለውን የመረጃ ክፍተት ከማጥበብ አኳያ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ፍላጎት መሟላት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል::

በ1995 በጀት ዓመት ለማካሄድ የታቀዱ ጥናቶች መሠረታዊ የሆኑ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃዎችን የሚያስገኙና ውጤታቸው ለአገር አቀፍና ለክልሎች የስታቲስቲክስ መረጃ መዳበር እንዲሁም ሌሎች ድርጅቶች ወደፊት ለሚያዘጋጇቸው ዕቅዶችና ለሚያካሂዷቸው ምርምሮች በመነሻነት እንደሚያገለግሉ ይታመናል:: በመሆኑም መ/ቤቱ ጥናቶቹን ለማካሄድ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የመንግሥትና የአጠቃላዩን ሕብረተሰብ ያልተቋረጠ ድጋፍ ይጠይቃል::

ይህ የአንድ ዓመት ዕቅድ የተዘጋጀው ከላይ የተጠቀሱትን አጠቃላይ እውነታዎች መሠረት በማድረግ ሲሆን፣ ዕቅዱ በ11 የተለያዩ ክፍሎች ቀርቧል:: ከእነዚህም:- ክፍል 1 መግቢያ ሲሆን፣ ክፍል 2 ደግሞ የመ/ቤቱን የ1994 በጀት ዓመት የስምንት ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማን ይዟል:: ክፍል 3 የ1995 ዕቅድ ዓላማዎችና የአፈጻጸም ስልቶችን የሚያሣይ ሲሆን፣ ክፍል 4 የ1995 ዕቅድ ይዘት ተብራርቷል:: በክፍል 5 ደግሞ ለታቀዱት

# የ1995 የስታቲስቲክስ ሥራ ዕቅድ

## 1. መግቢያ

መንግሥት ለሚወጥናቸው ዕቅዶችና ለሚያዘጋጃቸው ፕሮግራሞች በየዘርፉ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ሊገልጽ የሚችል ወቅታዊ፣ የተሟላና አስተማማኝ የሆነ ስታቲስቲካዊ መረጃ መኖር ወሣኝነት አለው:: በተጨማሪም እነዚህ መረጃዎች የታቀዱ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች በተግባር ላይ ሲውሉ ለመከታተልና ግምገማ ለማካሄድም ጠቃሚነታቸው የጎላ ሲሆን፣ በተለያዩ የኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ መስኮች ዙሪያ ለሚካሄዱ ጥናቶችና ምርምሮችም ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል::

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የአገሪቱን የስታቲስቲክስ መረጃ ፍላጎት በማሟላት ረገድ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣትና ለብሔራዊ ስታቲስቲክስ መረጃ ዕድገት አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በየጊዜው የተሻሻለ የአሠራር ዘዴዎች ላይ በመመርኮዝ የመንግሥትን የመረጃ ፍላጎትን ከፍተት ለማሟላት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፣ አሁንም በማካሄድ ላይ ይገኛል:: መ/ቤቱ ለዓላማው መሣካትም የተለያዩ ጥናቶችን በማካሄድና መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማቀነባበርና በመተንተን ሪፖርቶችን እያዘጋጀ ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት ላይ ይገኛል::

የባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንግሥትን የልማት የትኩረት አቅጣጫና የመረጃ ፍላጎትን ግምት ውስጥ በማስገባት እንደዚሁም የመ/ቤቱን የማስፈፀም አቅም በመገምገም በ1995 በጀት ዓመት ቅድሚያ ተሰጥቶአቸው ቢጠኑ ያለውን የመረጃ ክፍተት ከማጥበብ አኳያ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ፍላጎት መሟላት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል::

በ1995 በጀት ዓመት ለማካሄድ የታቀዱ ጥናቶች መሠረታዊ የሆኑ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃዎችን የሚያስገኙና ውጤታቸው ለአገር አቀፍና ለክልሎች የስታቲስቲክስ መረጃ መዳበር እንዲሁም ሌሎች ድርጅቶች ወደፊት ለሚያዘጋጇቸው ዕቅዶችና ለሚያካሂዷቸው ምርምሮች በመነሻነት እንደሚያገለግሉ ይታመናል:: በመሆኑም መ/ቤቱ ጥናቶቹን ለማካሄድ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የመንግሥትና የአጠቃላዩን ሕብረተሰብ ያልተቋረጠ ድጋፍ ይጠይቃል::

ይህ የአንድ ዓመት ዕቅድ የተዘጋጅው ከላይ የተጠቀሱትን አጠቃላይ እውነታዎች መሠረት በማድረግ ሲሆን፣ ዕቅዱ በ11 የተለያዩ ክፍሎች ቀርቧል:: ከእነዚህም:- ክፍል 1 መግቢያ ሲሆን፣ ክፍል 2 ደግሞ የመ/ቤቱን የ1994 በጀት ዓመት የስምንት ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማን ይዟል:: ክፍል 3 የ1995 ዕቅድ ዓላማዎችና የአፈጻጸም ስልቶችን የሚያሣይ ሲሆን፣ ክፍል 4 የ1995 ዕቅድ ይዘት ተብራርቷል:: በክፍል 5 ደግሞ ለታቀዱት

ጥናቶች ማስፈፀሚያ የሚውል የካፒታል በጀት ፍላጎትና መግለጫ ቀርቧል:: እንደዚሁም ከ6 እስከ 10 ድረስ ባሉት ክፍሎች ውስጥ የ1995 የካፒታል በጀት ፍላጎት በወጪ ዓይነት፣ የ1995 የዕቅድ ግብ፣ የሰው ኃይል ፍላጎት፣ የዕቅዱ መርሃ-ግብርና የካፒታል በጀት መጠየቂያ በቅደም ተከተል እንዲካተቱ ተደርጓል:: በመጨረሻም በክፍል 11 የ1995 ዕቅድን ተግባራዊ ለማድረግ በበላይ አካል ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች እንዲካተቱ ተደርጓል::

## 2. የ1994 የስምንት ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ

### 2.1 ብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራምን በተመለከተ

በ1994 በጀት ዓመት በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ስር አራት አዳዲስ ጥናቶችና ከ1993 ዓ.ም መረጃ ተሰብስቦላቸው የመረጃ ቅንብርና የሪፖርት ዝግጅት ተግባራቸው ወደ 1994 በጀት ዓመት የተሸጋገሩ ሁለት ነባር ጥናቶችን ለማጠናቀቅ በዕቅድ ይዞ ነበር:: በዚህም መሠረት እስከ የካቲት 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ባሉት ስምንት ወራት ውስጥ:-

#### ሀ/ አዳዲስ ጥናቶችን በተመለከተ

በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራች ዋጋ ጥናት የሐምሌና የነሐሴ ወር 1993 ዓ.ም መረጃ በግብርና ናሙና ቆጠራ የመስክ ሠራተኞች ሥልጠና ምክንያት ሳይከናወን ቀርቷል:: ቢሆንም ከመስከረም ወር 1994 ዓ.ም እስከ ጥር ወር 1994 ዓ.ም ድረስ ያለው መረጃ ተሰብስቦ የኤዲቲንግና ኮዲንግ እንደዚሁም የዳታ ኢንትሪና ክሊኒንግ ሥራ የተጠናቋል:: በተጨማሪም የየካቲት ወር የአምራቾች ዋጋ ጥናት መረጃ ደግሞ ከመስክ በመሰብሰብ ላይ ይገኛል::

በገጠር የሚካሄደው የችርቻሮ ዋጋ ጥናት መረጃ አገሪቱ በምትከተለው የነፃ ገበያ ስርዓት አንፃር ሲገመገም የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስን ለማስላት የተመረጡ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በእነዚህ የገጠር ገበያዎች በአብዛኛው ካለመገኘት ሣቢያ የገጠር ጥናቱ ተቋርጦ ከየዞኑ የደራ ገበያ ቦታዎችን ብቻ በመምረጥ ጥናቱ በእነዚህ አካባቢዎች ላይ እንዲካሄድ ተደርጓል:: በመሆኑም በ106 ከተሞች ውስጥ በሚገኙ 119 የገበያ ቦታዎች የሚካሄደው የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ከሐምሌ 1993 እስከ ኅዳር 1994 ዓ.ም ድረስ ባሉት ወራት የተሰበሰቡ መረጃዎች የኤዲቲንግና ኮዲንግ እንደዚሁም የዳታ ኢንትሪና ክሊኒንግ ሥራ ተጠናቋል:: የታህሣስ ወር 1994 ዓ.ም መረጃ የዳታ ክሊኒንግ ሥራ በመካሄድ ላይ ሲሆን የጥር ወር መረጃ ከመስክ ተሰብስቦ በዋናው መ/ቤት በመቀነባበር ላይ ነው::

የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ በነባር ገበያዎች ለውጥ ምክንያት ከ1993 በጀት ዓመት መጨረሻ (ሰኔ ወር ድረስ) ያለው ኢንዴክስ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል::

በተጨማሪም የበጀት ዓመቱ ኢንዴክስ ለአዲስ አበባ ከተማ እስከ ጥር ወር 1994 ዓ.ም ድረስ ያሉት መረጃዎች ለተጠቃሚዎች የተሰራጩ ሲሆን፣ የየካቲት ወር መረጃም በመቀነባበር ላይ ይገኛል። የታህሣሥ ወር 1993 ዓ.ም መሠረት ያደረገው አዲሱን ኢንዴክስ ለእያንዳንዱ ክልልና በአገር አቀፍ ደረጃ አዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት እንዲቻል በቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት ወቅት የተገኘውን የወጪ መጠን የመቶኛ ድርሻን ( weight ) በመውሰድ ክለሳውና ስሌቱ ተጠናቋል።

የ1993 ዓ.ም የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናትን ለማካሄድ የዝግጅት ሥራው ማለትም የመጠይቆች ሕትመትና የመረጃ ሰብሳቢዎች ምልመላ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ በመጋቢት ወር 1994 ዓ.ም የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ተጀምሯል።

ለ. <u>ነባር ጥናቶችን በተመለከተ</u>

መ/ቤቱ በ1993 በጀት ዓመት መረጃ ከተሰበሰበላቸው ጥናቶች የዋናው መኸር ወቅት የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል። እንዲሁም የዚሁ ዓመት የበልግ ወቅት የሰብል ምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት መረጃዎች ቀሪ ሥራዎች በሙሉ ከተጠናቀቁ በኋላ ሪፖርታቸው ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

የ1993 የቤት እንስሳት ጥናት የተሰበሰበው መረጃ የኤዲቲንግና ኮዲንግ እንደዚሁም የመረጃ ቅንብሩ ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

በ1993 ዓ.ም የመረጃ መሰብሰብ ተግባራቸው ተጠናቆ የመረጃ ማቀነባበሩ ሥራ ወደ 1994 ዓ.ም ከተላለፉ ነባር ጥናቶች መካከል ውስጥ የ1992 ዓ.ም የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት ቀሪ ሥራዎች በበጀት ዓመቱ ሁለተኛ ሩብ ዓመት ሙሉ በሙሉ ተጠናቆና ታትሞ ሪፖርቱ ለመረጃ ተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል።

የዓለም የሥራ ድርጅት (ILO) እና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር በጋራ የልጆች የሥራ ሁኔታ ጥናት በመ/ቤቱ እንዲካሄድ በጠየቁት መሠረት በ1993 በጀት ዓመት የመረጃ መሰብሰብ ተግባሩ ተካሂዷል። ይህ ጥናት በ1994 በጀት ዓመት የመረጃ ማቀነባበርና የሪፖርት ዝግጅት ተግባራት በመካሄድ ላይ ሲሆን በተለይ ሪፖርቱ አለማቀፋዊ ይዘት እንዲኖረው ለማድረግ አንድ ከILO በመጣ የወጪ አማካሪ ስለ ሪፖርቱ ቴክኒካዊ ይዘት ላይ ከመ/ቤቱ ባለሙያዎች ጋር ውይይትና የሥራ ልምድ ልውውጥ ተደርጓል።

## 2.2 የግብርና ናሙና ቆጠራን በተመለከተ

በአገራችን በዓይነቱ የመጀመሪያ ለሆነው የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ የዝግጅት ሥራ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ወራት ላይ ተጠናቆ ከመስከረም 2 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ የመረጃ መሰብሰቡ ተግባር የግብርና ቆጠራ ቦታዎችን ካርታ ወሰን በመለየትና የግብርና ቤተሰቦችንና የቤተሰብ ኃላፊዎችን በመመዝገብ ተጀምሯል፡፡ በበጀት ዓመቱ ባለፉት ስምንት ወራት ውስጥ፡-

ሀ. የግብርና ናሙና ቆጠራ የሰብል ትንበያ መረጃ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ይህ ጥናት በአገሪቱ ላሉ ዞኖች ወካይነት ባለው ሣይንሣዊ መንገድ በናሙና በተመረጡ 1928 የቆጠራ ቦታዎች ተሸፍኗል፡፡ ከነዚህ የቆጠራ ቦታዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች የመረጃ ቅንብር ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቱ ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

ለ. የግብርና ናሙና ቆጠራው አንዱ አካል የግብርና ቤተሰቦች ዲሞግራፊያዊና ኢኮኖሚያዊ ባሕሪያት መረጃ ሲሆን፣ ይህም ሥራ በመስክ የመረጃ መሰብሰቡ ተግባር ተጠናቆ የመረጃ ማቀነባበሪያ ተግባር በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ሐ. የግብርና ናሙና ቆጠራ ክፍል የሆነው የዋናው መኸር የመስክ ሥራ ማለትም የታረሰ መሬት ስፋት፣ የሰብል ምርት መጠን፣ የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ፣ የመሬት አጠቃቀም እንዲሁም የቤት እንስሳት የዶሮና የንብ ቀፎዎች ብዛትና የማር ምርት መጠን መረጃዎች ከመስክ ተሰብስበው በዋናው መ/ቤት የገቡ ሲሆን፣ በወጣላቸው መርሃ-ግብር መሠረት እንደቅደም ተከተላቸው የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ እየተካሄደ ይገኛል፡፡

መ. የግብርና ናሙና ቆጠራ አንዱ አካል የሆነው የከተማ አካባቢ ግብርና ናሙና ቆጠራ በአገሪቱ በሚገኙ 842 ከተሞች ውስጥ በተመረጡ ከ4200 የቆጠራ ቦታዎች ላይ መረጃ ተሰብስቦ መጠይቁ ዋናው መ/ቤት ገብቷል፡፡

ሠ. በአርብቶ አደሩ አካባቢ (በአፋርና በሶማሌ ክልል) ለሚካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ ጥናት ለተከታታይ ዓመታት ግመገማ ተካሂዷል፡፡ የግምገማው ዓላማ በነዚህ አካባቢዎች ቆጠራ በየትኛው ወቅትና በየትኛው ዘዴ ቢካሄድ የተሟላ መረጃ ማግኘት ይቻላል የሚል ሲሆን፣ በግምገማው መሠረት በአፋር አካባቢ ከመስከረም እስከ ጥቅምት ወር 1995 ዓ.ም እንደዚሁም በሶማሌ አካባቢ ከጥቅምት እስከ ኅዳር ወር 1995 ዓ.ም ድረስ ይካሄዳል፡፡

በሌሎች የአርብቶ አደሩ አካባቢዎች ( ከአፋርና ከሶማሌ ክልል ውጪ የሆኑ) በ1994 በጀት ዓመት አስፈላጊው መረጃ የሚሰበሰብላቸው ሲሆን፣ በአጠቃላይ የግብርና ናሙና ቆጠራው ሥራ ሲገመገም የመስክ እንቅስቃሴውና በቢሮ የሚከናወኑ ተግባራት በወጣላቸው መርሃ-ግብር መሠረት እየተከናወኑ ይገኛሉ።

## 2.3 የሰው ኃይል ቅጥርና ሥልጠናን በተመለከተ

በ1994 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በባለሥልጣኑ መ/ቤት 1,480 ቋሚና 1,665 የኮንትራት በጠቅላላው 3,145 ሠራተኞች ሠራተኞች ነበሩ። በበጀት ዓመቱ ለመቅጠር ከታሰበው ተጨማሪ የሰው ኃይል እስከ የካቲት 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ 41 ቋሚና 14,663 የኮንትራት በድምሩ 14,704 ሠራተኞች ተቀጥረዋል። ከዚህም ሌላ ከቋሚ ሠራተኞች 63 እንዲሁም ከኮንትራት ሠራተኞች 264 በድምሩ 327 ሠራተኞች በተለያዩ ምክንያት ከነበረው የሰው ኃይል የተቀነሱ በመሆናቸው በበጀት ዓመቱ ስምንተኛ ወር መጨረሻ ላይ የነበረው የሰው ኃይል 1,458 ቋሚና 16,064 የኮንትራት በድምሩ 17,522 ሠራተኞች ናቸው።

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በየጊዜው ለሚያካሂዳቸው አዳዲስና ነባር ጥናቶች ያሉትን ባለሙያዎች ወቅታዊ የሆነ ሥልጠና በመስጠት ሙያቸውን እንዲያዳብሩ ያደረገ ሲሆን፣ በ1994 በጀት ዓመት የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ተከናውኗል።

ሀ. በአዲስ መልክ ለተጀመረው የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ከመላው አገሪቱ ከተመረጡ 119 የገበያ ቦታዎች መረጃ ለሚሰበስቡ ሠልጣኞች ከሰኔ 20 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ሳምንት ሥልጠና በዋናው መ/ቤት የተሰጣቸው ሲሆን፣ ሠልጣኞቹም ወደተመደቡበት የገበያ ቦታ ተሠማርተው ወርሃዊ መረጃ በመሰብሰብ ላይ ይገኛሉ።

ለ. በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ በአዲስ አበባ በሁለት ማሰልጠኛ ማዕከላት ከዋናው መ/ቤት፣ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ከሌሎች መ/ቤቶች ለተውጣጡ 542 ባለሙያዎች ከሰኔ 5 ቀን 1993 እስከ ሰኔ 29 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ የአሠልጣኞች ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ በተመሣሣይ ሁኔታ ከሐምሌ 13 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 23 ቀን 1993 ዓ.ም በ47 የተመረጡ የሥልጠና ማዕከላት ለ13,100 የመረጃ ሰብሳቢዎችና ለ2,430 ተቆጣጣሪዎች ሥልጠና በመስጠት፣ ነሐሴ 24 ቀን 1993 ዓ.ም በማዕከል በተዘጋጀ የመመዘኛ ፈተና ውጤት መሠረት ብቃት ያላቸው ለመስክ ሥራው ተመርጠው በሥራ ላይ ይገኛሉ።

ሐ. በ1993 ዓ.ም ለአንድ ዓመት በጋና ሀገር የማስተርስ ዲግሪ ትምህርት የተከታተሉ ሁለት ባለሙያዎች ትምህርታቸውን ጨርሰው የተመለሱ ሲሆን፣ በተመሳሳይ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከነበሩት መካከል ሦስቱ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደሥራ ተሰማርተዋል:: እንዲሁም ሌሎች ሦስት ባለሙያዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ::

መ. በበጀት ዓመቱ ስምንት ወራት የመ/ቤቱን ሠራተኞች የሥራ ብቃት ለማሻሻል በነበረው ዕቅድ መሠረት ሦስት ሠራተኞች ለ5 ቀናት የቢሮ አያያዝ ሥልጠና፣ 2 ሠራተኞች በሰው ኃይል አደረጃጀት፣ 2 ሠራተኞች በዘመናዊ የማኅደር አያያዝ፣ አንድ ሠራተኛ በውስጥ ቁጥጥር እያንዳንዳቸው ለአሥራ ሁለት ቀናት በኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲቲዩት እንዲሰለጥኑ የተደረገ ሲሆን፣ አንድ ሠራተኛ ደግሞ የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን በሚሰጠው የመካኒክነት ስልጠና ከኅዳር 24/1994 ዓ.ም ጀምሮ የሁለት ወር ስልጠና ተከታትሏል::

## 2.4 የፋይናንስ አጠቃቀምን በተመለከተ

ለባለሥልጣኑ መ/ቤት ከመንግሥት በ1994 በጀት ዓመት የተፈቀደለት ካፒታል በጀት ብር 135,364,700 ነው:: ከዚህ ውስጥ ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር 3,383,900 ሲሆን፣ ለግብርና ናሙና ቆጠራ ፕሮግራም ደግሞ ብር 131,980,800 ተፈቅዷል::

ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ከተፈቀደው በጀት ውስጥ እስከ የካቲት 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ብር 1,680,700 ወጪ ተደርጓል:: አፈፃፀሙም ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ጋር ሲነፃፀር 49.7 በመቶኛ ነው:: ከተፈቀደው በጀት በልዩነት የሚታየው ለቀሪ ሥራዎች ማስፈፀሚያ የሚውል ይሆናል::

ለግብርና ናሙና ቆጠራ ከተፈቀደው ብር 131,980,800 ብር ውስጥ እስከ የካቲት 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ ብር 96,562,900 ወጪ ተደርጓል:: ይህም ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው በጀት ወጪ የሆነው 73.2 በመቶ ሲሆን፣ ቀሪው በጀት በሚቀጥሉት ወራት መ/ቤቱ ለሚያከናውናቸው ሥራዎች ማስፈፀሚያ የሚውል ይሆናል::

## 2.5 በ1994 ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ያጋጠሙ ችግሮች

ሀ. የባለሥልጣኑ መ/ቤት በበጀት ዓመቱ በመላው አገሪቱ የጀመረው የግብርና ናሙና ቆጠራ ተግባር ከፍተኛ የሆነ የሰው ኃይል በመጠየቁ በተለይም ለመስክ ሠራተኞች ትኩረት በመስጠት ከአጎራባች ክልሎችና ዞኖች ለመቅጠር ተሞክሯል:: ሆኖም

መ/ቤቱ የቆጠራ ሥራውን ለማቃናት ቀድሞ ከነበሩት 22 ቅ/ጽ/ቤቶች በተጨማሪ 25 ጽ/ቤቶች ከፍቶ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን፣ ለእነዚህና ለቀድሞዎቹ ጽ/ቤቶች የድጋፍ ሰጪ (የአስተዳደርና የፋይናንስ ሥራ) ሠራተኞችን ለመቅጠር ተሞክሮ እስከ አሁን ለማሟላት አልተቻለም:: በመሆኑም ጽ/ቤቶቹ ባልተሟላ የሰው ኃይል እየተንቀሳቀሱ ሲሆን፣ የቴክኒኩን ሥራ እንዲያስተባብሩ የተመደቡ ባለሙያዎች የአስተዳደሩን ሥራ ደርበው እንዲሰሩ በመደረጉ አስፈላጊ ያልሆነ የሥራ ጫና ፈጥሯል፣

ለ. በየጊዜው እያደገ የመጣው የመ/ቤቱ የሰው ኃይል ለማስተናገድ የሚችል ተጨማሪ ቢሮ ማግኘት አልተቻለም:: ይህ ችግር በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶችም በመኖሩ በየአመቱ ለኪራይ 308,856 ብር በላይ ወጪ ያደርጋል:: በተለይም ደግሞ ቅ/ጽ/ቤቶች ለተለያዩ ጥናቶች አገልግሎት የሚውሉ የመስክ መገልገያ መሣሪያዎች ማከማቻ ቦታ ያላቸው ለጽ/ቤት የሚሆኑ ቤቶችን በኪራይ ስለማያገኙ አንዳንድ ተጨማሪ ጊዜያዊ መጋዘኖች ማሠራትን በመጠየቁ ለማያስፈልግ ውጪ መ ቤቱ እየተዳረገ ሲሆን፣ በሥራውም ላይ ተፅዕኖ አሣድሯል::

ሐ. በባለሥልጣኑ መ/ቤት አሁን ያለው አወቃቀር በተወሰነ የሰው ኃይል በተደራጀ አንድ መምሪያ አማካይነት 22 ቅ/ጽ/ቤቶችን ከዋናው መ/ቤት ለመቆጣጠርና ለመምራት እየተሞከረ ነው:: ይህም አሠራር በፈጠረው የሥራ ብዛት ምክንያት የመ/ቤቱን የበላይ ኃላፊዎች ተጨማሪ የሥራ ጫና በሚፈጥር መልኩ ከተሰጣቸው ኃላፊነት ውጪ እንዲሰሩ በማድረግ በመደበኛ ተግባራቸው ላይ ተፅዕኖ አሣድሯል::

## 3. የ1995 የሚካሄዱ ጥናቶች ዕቅድ ዓላማዎችና የአፈፃፀም ስልቶች

### 3.1 በ1995 የሚካሄዱ ጥናቶች ዓላማዎች

በ1995 የሚካሄዱ ጥናቶች ዕቅድና ዓላማዎች ከመ/ቤቱ አበይት ተግባራት ጋር የተቀናጁ ሆነው የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ::

ሀ. ለፕላን ዝግጅት፣ ለክትትልና ግምገማ፣ ለምርምር፣ ለፖሊሲ ቀየሳና ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች ሊያገለግሉ የሚችሉ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና የዲሞግራፊ መረጃዎችን በተቀናጀ አሠራር ሰብስቦ፣ አቀነባብሮና ተንትኖ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣

ለ. በስታቲስቲክስ ሥራ አኳያ በሌሎች መሥሪያ ቤቶች የስታቲስቲክስ መዝገብ አያያዝና የሪፓርት ሥርዓት እንዲዘረጋ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣

ሐ. ወደፊት የሚኖረውን ሰፊ የስታቲስቲክስ የመረጃ ፍላጎት ከማሟላት አኳያ አመቺና ተስማሚ የሆኑ የስታቲስቲክስ ሥራዎች ማከናወኝ፡

## 3.2 የ1995 ዕቅድ የአፈፃፀም ስልቶች

ሀ. የአገሪቷ የስታቲስቲክስ ሥራ ጥራትና ደረጃው የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ይቻል ዘንድ የባለሥልጣኑ መ/ቤት አቅሙን ለማጎልበት ጥረት ማድረግ፡

ለ. ከተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ጋር የሚኖረውን የሥራ ግንኙነት በማጠናከር በተለይም ሕብረተሰቡ የስታቲስቲክስ መረጃ አስፈላጊነትና ጥቅም በሚገባ ተረድቶ ትክክለኛ መረጃ በመስጠት ረገድ ትብብር እንዲያደርግ በተለያዩ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ተገቢውን ትምህርትና ቅስቀሳ ማድረግ፡

ሐ. የስታቲስቲክስ የአሠራር ዘዴን በማሻሻል የመረጃ መሰብሰብ፣ ቅንብርና ትንተና ሥራ በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይል ስለሚያስፈልግ በዚህ በኩል የሚመደብ ሠራተኛ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር እንዲሰለጥን ማድረግ፡

መ. የባለሥልጣኑ መ/ቤት ከተለያዩ የውጭ አገር መንግሥታት፣ የዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር በቀጥታም ሆነ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት በኩል ግንኙነት በመፍጠርና ብሎም በማጠናከር ጥናት ማካሄድ፣ የሥልጠናና የፋሲሊቲዎች ድጋፍ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ናቸው፡፡

## 4. የ1995 ዕቅድ ይዘት

በ1995 በጀት ዓመት በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም በዛ ያሉ ጥናቶች የተካተቱ ሲሆን፤ ለዚህም የባለሥልጣኑ መ/ቤት ያለውን የሠለጠነ የሰው ኃይል ሎጂስቲክስና የፋይናንስ አቅም በማቀናጀት ለማከናወን አቅዷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በ1994 የመረጃ መሰብሰብ ተግባር የተጠናቀቀላቸው የግብርና ናሙና ቆጠራ መረጃዎች በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ በማጠናቀር፣ በመገምገምና የቆጠራ ውጤት የሚያሣዩ ሪፖርቶች ይዘጋጃሉ፡፡ እንደዚሁም በአፋርና በሶማሌ ክልል የሚካሄደው የአርብቶ አደሩ አካባቢ ግብርና ናሙና ቆጠራ ሥራ ይከናወናል፡፡ በመሆኑም በ1995 ዓ.ም የስታቲስቲክስ ፕሮግራም መሠረት በዕቅድ ዓመቱ መጠናት ያለባቸው ጥናቶች ዝርዝር የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

ሀ. ብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት /በገጠር/
- የግብርና ግብአቶችና አሠራር ( Practices ) ጥናት /በገጠር /
- የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት /በገጠር/
- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት/በተመረጡ ገበያዎች/
- የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት/በከተማ/
- አነስተኛና የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት/በከተማና በገጠር/
- የዕደ-ጥበብና የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ጥናት/በገጠርና በከተማ/
- የኮንስትራክሽን ጥናት/በከተማ/
- የአከፋፋይ ንግድና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት/በከተማ/
- የተፈበረኩ ዕቃዎች የአምራቾች ዋጋ ሙከራ ጥናት/በከተማ/
- የጅምላ ዋጋ ሙከራ ጥናት / በከተማ/
- የኢንዴክሶች ዝግጅት ሥራ /በዋናው መ/ቤት/
- መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናት/በከተማ/ ናቸው።

ለ. የግብርና ናሙና ቆጠራ ቀጣይ ሥራዎች

- የአርብቶ አደሩ አካባቢዎች የሚካሄድ የግብርና ቆጠራ ማካሄድ፣ እና
- በአርሶ አደሩ አካባቢ በ1994 የተካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ የመረጃ ማቀነባበርና ሪፖርት የማዘጋጀት፣ የማተምና የማሰራጨት ተግባራት ይከናወናሉ።

## 5. የ1995 ዓ.ም የካፒታል በጀት ፍላጎትና መግለጫ

### 5.1 የካፒታል በጀት ፍላጎት

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1995 በጀት ዓመት ለሚያካሂዳቸው የተለያዩ ጥናቶች ማስፈፀሚያ ማለትም ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም 31.4 ሚሊዮን ብር እንደዚሁም በ1994 በአርሶ አደሩ አካባቢዎች በተካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ የተሰበሰቡ መረጃዎች ኤዲትና ኮድ የማድረግና ኮምፒውተር ውስጥ አስገብቶ በማቀነባበርና በመገምገም የሪፖርት ዝግጅትን የማከናወንና በተጨማሪም የአርብቶ አደሩ አካባቢ ግብርና ናሙና ቆጠራ ለማካሄድ ብር 14.1 ሚሊዮን የሚያስፈልግ ሲሆን በጠቅላላው 45.5 ሚሊዮን ብር እንደሚደርስ ተገምቷል።

5.2 <u>የካፒታል በጀት ፍላጎት መግለጫ</u>

በ1995 በጀት ዓመት በባለሥልጣኑ መ/ቤት ለሚጠኑ ጥናቶች የተያዘው በጀት የመ/ቤቱን የሰው ኃይል፣ ሎጂስቲክስና ሌሎች ለሥራው አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ የተባሉ ቅድመ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ሲሆን፣ እንደሥራው ሁኔታ አዲስ የሚቀጠሩ ባለሙያዎችንና የመስክ ሠራተኞችን ግምት ውስጥ በማስገባት የበጀት ፍላጎት ዝርዝር የተሰላው ቀጥሎ ያሉትን ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ በማካተት ነው፡፡

5.2.1 መረጃ የሚሰበሰብባቸው የቆጠራ ቦታዎች በገጠር 2023 እና በከተማ 535 በድምሩ 2558 ሲሆኑ፣ ለትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ ለአነስተኛና የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ ለዕደ ጥበብና ጎጆ ኢንዱስትሪዎች፣ ለኮንስትራክሽን ጥናት፣ ለአከፋፋይና አገልግሎት ሰጪ ንግድ ድርጅቶች ጥናት በየድርጅቶቹ መረጃዎች ይሰበሰባሉ፡፡

5.2.2 የግብርና ናሙና ቆጠራ ሪፖርት ዝግጅት የሚካሄደው በወረዳ ደረጃ ሲሆን፣ የሌሎች ጥናቶች ግን እንደአስፈላጊነቱ በከተማ፣ በዞን ወይም በአገር አቀፍ ደረጃ ይሆናል፡፡

5.2.3 በደመወዝ የወጪ አርዕስት የተጠቀሰው የሰው ኃይል በሙሉ በኮንትራት ቅጥር የሚሟላ እንጂ መደበኛ ወይም ቋሚ ሠራተኞችን አይጨምርም፡፡ ሆኖም የቋሚ ሠራተኞች ወጪ በቁጥጥርና በሥልጠና ወቅት ለሚሳተፉት የሚከፈላቸው የውሎ አበልና እንዳስፈላጊነቱ ለሌሎች ወጪዎች በፕሮጀክቱ ሂሣብ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

5.2.4 ለወጪ ቅነሳና እንዲሁም የሰው ኃይል ጉልበት በአግባቡ ለመጠቀም ኤዲተሮችና የመረጃ ኢንኮደሮች በሚወጣላቸው ፕሮግራም መሠረት በተናጠል ወይም በጋራ የሁሉንም ጥናቶች መረጃዎች ኤዲትና ኮድ የሚደረጉ ሲሆን፣ መረጃ ኢንኮደሮችም መረጃዎችን ወደ ኮምፒዩተር ውስጥ ያስገባሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም በሥልጠናና በመስክ ቁጥጥር ወቅት ለሁሉም ጥናቶች የመስክ መኪናዎች አጠቃቀም በጋራ ይሆናል፡፡ እንደዚሁም ከዋናው መ/ቤት የኤክስፐርት ተቆጣጣሪዎች ስምሪት በቅንጅት ለገጠርና ለከተማ ጥናቶች ይሆናል፡፡

5.2.5 በጽሕፈት መሣሪያዎችና በሕትመት የወጪ ርዕስ የተገለጸው አኃዝ ለጥናቶቹ የሚያስፈልገውን የሚያጠቃልል ሲሆን በዝርዝር ሲገለጽ ለጥናቶቹ ለሚሰማራው የሰው ኃይል የሚያስፈልገው የጽሕፈት መሣሪያዎች ማለትም እርሳስ፣ መቅረጫ፣ ላፒስ፣ እስክሪፕቶ፣ ማስታወሻ ደብተር፣ ክላሰር... ወዘተ ሲሆኑ፣ በሕትመት ወጪ የሚጠቃለሉ ደግሞ ለመመሪያዎች፣ ለተለያዩ መጠይቆችና ቅጾች እንደዚሁም

ለሪፓርቶች ዝግጅት የሚሆን የወረቀት ብዛትና ኬሚካሎች የሚገዙበት ዋጋ ተተምኖ የተሰላ ነው:: ሌሎች ወጪዎች ደግሞ በበጀት ዓመቱ ከሚካሄዱት ፕሮጀክቶች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ያላቸው በመሆናቸው የቀረቡ ይገኛሉ:: እነዚህም

ሀ/ ለ22ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ቢሮ፣ የሥልጠና አዳራሽና የመጋዘን ኪራይ

ከ22ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል 6ቱ በመንግሥት ቤት በነፃ 16ቱ ደግሞ ለግለሰብና ለኪራይ ቤቶች አስተዳደር በዓመት ብር 308,856 ኪራይ እየተከፈለላቸው ሥራቸውን ያከናውናሉ:: ከነዚህ በተጨማሪ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች በ1995 በአዲስ ሁኔታ የሚከፈቱ ሲሆን፣ ለእነዚህ ጽ/ቤቶች በዓመት ብር 72,000 የቢሮ ኪራይ የተያዘላቸው ሲሆን፣ በያአካባቢው ለሚካሄደው ጥናት ላይ ለሚሣተፉ የመስክ ሠራተኞች የሥልጠና አዳራሾች እንዲሁም አብዛኛዎቹ ጽ/ቤቶች የተከራዩት ቢሮ ጠባብ ስለሆኑ፣ ያላቸውን ሎጂስቲክስና ቁሣቁስ ለማከማቸት በቂ ባለመሆናቸው ለእነዚህ አገልግሎት የሚውሉ መጋዘኖች ኪራይ ተጠይቋል::

ለ/ ለሠራተኞች የአደጋ ኢንሹራንስ

በሕዝብና ቤት ቆጠራዎች ወቅትና በተለያዩ ጊዜያት የመ/ቤቱ ሠራተኞች በሥራ ላይ የሕይወትና የአካል ጉዳት ስለደረሰባቸው በዚሁ ተመክሮ ለመስክ ሥራ ለሚንቀሳቀሱ ሠራተኞች የአደጋ ኢንሹራንስ ሽፋን እንዲያገኙ ታምኖበት ባለፉት ዓመታት ተግባራዊ ሆኖ ተጎጂ ሠራተኞች ተጠቃሚ ሆነዋል:: በተመሳሳይ ሁኔታ በመስክ ሥራ የሚሠማሩ ሠራተኞች በሙሉ የአደጋ ኢንሹራንስ ሽፋን እንዲያገኙ ታስቦ የቀረበ በጀት ነው::

ሐ/ ለሠራተኞች አጫጭር ስልጠና መስጠት

በመ/ቤቱ የሚሠሩ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በየጊዜው ያላቸውን ሙያ እንዲያሻሽሉና እንዲያጎለብቱ እንዲሁም ከአዳዲስ አሠራሮች ጋር እንዲተዋወቁ ለማድረግ በየጊዜው በአገር ውስጥ በሚገኙ ማሰልጠኛዎች የአጭር ጊዜ ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ በበጀት ዓመቱ ለሚካሄዱ ስልጠናዎች በጀት ጠይቋል:: እነዚህም ስልጠናዎች በተለይም ደግሞ አዲስ በተፈቀዱ የሥራ መደቦች ላይ ለሚመደቡ የመ/ቤቱ አዲስና ነባር ሠራተኞች ስልጠና ላይ የሚያተኩሩ ይሆናሉ ተብሎ በዕቅዱ ተይዟል::

## 6. የ1995 የካፒታል በጀት ፍላጎት በወጪ ዓይነት

ለ1995 በጀት ዓመት የባለሥልጣኑ መ/ቤት ለሚያካሂዳቸው ሁለት ፕሮግራሞች በጠቅላላው 45,496,349 ሚሊዮን ብር የካፒታል በጀት ጥያቄ ያቀረበ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ለብሔራዊ የተቀናጀ ስርቬይ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ 31,357,961 ሚሊዮን ብር እንዲሁም ለአርብቶ አደሩ አካባቢ ግብርና ናሙና ቆጠራ የመረጃ የመሰብሰብ ተግባራት ለማከናወንና በ1994 በአገሪቱ በአርሶ አደሩ አካባቢዎች በግብርና ናሙና ቆጠራ የተሰበሰቡ በርካታ መረጃዎችን ኢዲትና ኮድ ለማድረግ እንደዚሁም መረጃውን ኮምፒውተር ውስጥ በማስገባት ብሎም መረጃውን ለማቀነባበርና ሪፖርት ዝግጅት 14,138,388 ሚሊዮን ብር ያስፈልጋል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

## 6.1 ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የበጀት ፍላጎት ማጠቃለያ

6.1.1 ለደመወዝ ---------- ብር 8,142,036

6.1.2 ለሰው ጉልበት ወጪ ---------- ብር 576,030

6.1.3 ለአበል ---------- ብር 594,738

- ለበረሃ አበል ---------- ብር 187,398
- ለመጠሊያ አበል ---------- ብር 407,340

6.1.4 ለአላቂ የጽ/መሣሪያዎች ---------- ብር 370,000

6.1.5 ለሕትመት ---------- ብር 120,000

6.1.6 ለነዳጅና ቅባቶች ---------- ብር 3,987,390

6.1.7 ለውሎ አበል ---------- ብር 10,449,965

- ለሥልጠና ---------- ብር 4,163,119
- ለመስክ ሥራ ---------- ብር 6,286,846

6.1.8 ለትራንስፖርት ክፍያ ---------- ብር 857,2[illegible]0

- ለተሽከርካሪ ---------- ብር 613,630
- ለበቅሎ ---------- ብር 243,600

6.1.9 ለተሽከርካሪ ጥገና ---------- ብር 3,890,500

- ለተሽከርካሪ ጥገና ---------- ብር 3,012,000
- ለጎማ ግዢ ---------- ብር 878,500

6.1.10 ለቋሚ ዕቃዎች ጥገና ---------- ብር 160,000

6.1.11 ለኪራይ ---------- ብር 440,856

- ለጽ/ቤቶች ኪራይ ---------- ብር 380,856
- ለሥልጠና አዳራሽ ኪራይ ---------- ብር 60,000

6.1.12 ለኢንሹራንስ ---------- ብር 1,019,216

- ለተሽከርካሪዎች ---------- ብር 496,980
- ለመስክ ሠራተኞች ---------- ብር 522,236

6.1.13 ለኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ ---------- ብር 60,000

6.1.14 ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ክፍያ ---------- ብር 360,000

6.1.15 ለውሃ፣ ፖስታና ሌሎች አገ/ክፍያ ---------- ብር 90,000

6.1.16 ለአገር ውስጥ ሥልጠና ---------- ብር 150,000

6.1.17 ለቋሚ ዕቃዎች ግዢ ---------- ብር 90,000

ድምር ---------- ብር 31,357,961

6.2 <u>ለግብርና ናሙና ቆጠራ ቀጣይ ሥራዎች</u>

ለአርብቶ አደሩ አካባቢ ግብርና ናሙና ቆጠራ የመረጃ መሰብሰብ ተግባራትን ለማከናወንና በ1994 በአርሶ አደሩ አካባቢዎች በግብርና ናሙና ቆጠራ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ማቀነባበርና የሪፖርት ዝግጅት የበጀት ፍላጎት ማጠቃለያ:-

6.2.1 ለደመወዝ ---------- ብር 4,131,372

6.2.2 ለሰው ጉልበት ወጪ/ለመንገድ መሪና አስተርጓሚ/ ---------- ብር 4,850,400

6.2.3 ለአበል ---------- ብር 584,960

- ለበረሃ አበል ---------- ብር 488,960
- ለመጠለያ አበል ---------- ብር 96,000

6.2.4 ለአላቂ የቢሮ ዕቃዎች ---------- ብር 104,000

6.2.5 ለሕትመት ---------- ብር 175,000

6.2.6 ለነዳጅና ቅባቶች ---------- ብር 148,350

6.2.7 ለውሎ አበል ---------- ብር 1,996,686

- ለመስክ ሥራና ---------- ብር 1,778,466
- የቆጠራውን ውጤት ይፋ ለማድረግ ለማስተዋወቂያ ሴሚናር ---------- ብር 188,220

6.2.8 ለትራንስፖርት ክፍያ ---------- ብር 721,600

- ለተሽከርካሪ ---------- ብር 395,200
- ለበቅሎ ---------- ብር 326,400

6.2.9 ለመስተንግዶ ---------- ብር 150,000

6.2.10 ለትራንስፖርት ጥገና ---------- ብር 299,000

- ለተሽከርካሪ ጥገና ---------- ብር 138,000
- ለተሽከርካሪ ጎማ ግገር ---------- ብር 161,000

6.2.11 ለማስታወቂያ አገልግሎት ---------- ብር 250,000

- ለበራሪ ወረቀቶች ዝግጅት ---------- ብር 200,000
- ለትምህርትና ቅስቀሳ ---------- ብር 50,000

6.2.12 ለኢንሹራንስ ---------- ብር 757,020

- ለተሽከርካሪዎች ---------- ብር 182,160
- ለመስክ ሠራተኞች ---------- ብር 574,860

ድምር ---------- ብር <u>14,138,388</u>

# የ1995 የብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የካፒታል በጀት ፍላጎት

ሠንጠረዥ 1

| የወጪዎች ዝርዝር በወጪ አርዕስት | የስታቲስቲክስ ጥናቶች ዓይነት | | |
|---|---|---|---|
| | ገጠር | ከተማ | |
| | . የሰብል ትንበያ ጥናት<br>. የግብርና ግብአቶች አጠቃቀም ጥናት<br>. የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት<br>. የዕቃዎችና የአገል. የችርቻሮ ዋጋ ጥናት<br>. የዕደ ጥበብና የጎጆ ኢንዱስትሪ ጥናት<br>. የአነስተኛ የማምረቻ ኢንዱ.ጥናት | . የትላል. የመካከ.ማምረቻ ኢንዱስ. ጥናት<br>. የኮንስትራክሽን ጥናት<br>. የአከፋፋይ ንግድና አገ/ሰጪ ድርጅቶች ጥናት<br>. የአነስተኛ የማምረቻ ኢንዱ.ጥናት<br>. የዕደ ጥበብና የጎጆ ኢንዱስትሪ ጥናት<br>. መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዝርፍ ጥናት | . የዕቃዎችና የአገል.የችርቻሮ ዋጋ ጥናት<br>. የተፈበረኩ ዕቃዎች አምራች ዋጋ ጥናት<br>. የኢንዴክሶች ዝግጅት<br>. የጅምላ ዋጋ ሙከራ ጥናት |
| I. ደመወዝ | | | |
| . ለጀማሪ ፕሮፌሽናሎች | 28x895x12= 300,720 | - | - |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች* | - | 110x450x4= 198,000 | - |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች | 1568x381x6= 3,584,448 | 562x381x6= 1,284,732 | 120x381x12= 548,640 |
| . ለመስክ ተቆጣጣሪዎች | 154x630x6= 582,120 | 107x630x6= 404,460 | - |
| . ለዳታ ኢንትሪ ሱፐርቫይዘሮች (ለቅ/ጽ/ቤቶች) | 11x630x12= 83,160 | | - |
| . ለኤዲተሮች | 20x530x12= 127,200 | | - |
| . ለዳታ ኢንትሪ ኦፕሬተሮች | 30x450x12= 162,000 | | - |
| . ለዳታ ኢንትሪ ኦፕሬተሮች (ለቅ/ጽ/ቤቶች) | 11x450x12= 59,400 | | - |
| . ለሾፌሮች | 150x381x12= 685,800 | | - |
| . ፐርሶኔል | 3x760x12= 27,360 | | - |
| . ሂሣብ ሠራተኛ | 3x530x12= 19,080 | | - |
| . ገንዘብ ያዥ | 3x450x12= 16,200 | | - |
| . ንብረት ክፍል ሠራተኛ | 3x450x12= 16,200 | | - |
| . ፀሐፊ | 3x381x12= 13,716 | | - |
| . ተላላኪ | 3x200x12= 7,200 | | - |
| . ፅዳት ሠራተኛ | 3x200x12= 7,200 | | - |
| . ዘበኛ | 6x200x12= 14,400 | | - |
| **ንዑስ ድምር** | **5,706,204** | **1,887,192** | **548,640** |
| II የሰው ጉልበት ወጪ | | | |
| . ለሜትር ጎታችና ለመንገድ መሪ | 2023x210 x1= 424,830 | - | 120x70x12= 100,800 |
| . ለቀን ሙያተኞች | 20x210x12= 50,400 | - | - |
| **ንዑስ ድምር** | **475,230** | - | **100,800** |

* ለትላልቅና ለመካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች እና ለኮንስትራክሽን ጥናት የሚቀጠሩ ናቸው::

| | | | |
|---|---|---|---|
| III [illegible] | | | |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች የበረሃ አበል | 193x115x6= 133,170 | | 13x115x12= 17,940 |
| . ለተቆጣጣሪዎች " " | 32x189x6= 36,288 | | - |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች የመጠለያ አበል | 2023x30x6= 364,140 | | 120x30x12= 43,200 |
| ንዑስ ድምር | **533,598** | | **61,140** |
| **IV የጽ/መሣሪያና የኮምፒውተር አላቂ ዕቃ** | | | |
| . ለዋናው መ/ቤት | 150,000 | 100,000 | - |
| . ለቅ/ጽ/ቤቶች | 25x400x12= 120,000 | - | - |
| ንዑስ ድምር | **270,000** | **100,000** | - |
| **V. ለሕትመት** | | | |
| . ለኬሚካልና ለቀለም | **120,000** | - | - |
| **VI ነዳጅና ቅባት** | | | |
| ሀ/ ለሥልጠና | | | |
| . በዋናው መ/ቤት | 16x20x10x4.30= 13,760 | 12x20x10x4.30= 10,320 | 8x20x10x4.30= 6,880 |
| . በቅ/ጽ/ቤቶች | 25x10x10x4.30= 10,750 | 25x10x10x4.30= 10,750 | 25x10x10x4.30= 10,750 |
| ለ/ ለመስክ ሥራ | | | |
| . ከዋናው መ/ቤት ለሚሰማሩ ነዳጅ | 25x90x40x4.30= 387,000 | 25x90x20x4.30= 193,500 | - |
| . ከቅ/ጽ/ቤቶች ለሚሰማሩ ነዳጅ | 150x120x30x4.30= 2,322,000 | 132x90x20x4.30= 1,021,680 | - |
| ንዑስ ድምር | **2,733,510** | **1,236,250** | **17,630** |
| **VII ውሎ አበል** | | | |
| ሀ/ ለሥልጠና I | | | |
| . የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናቶች | | | |
| . የዋጋ ጥናቶች | | | |
| . የዕደ ጥበብና የጎጆ ኢንዱ.ጥናት | | | |
| በዋናው መ/ቤት ለሚሰጥ ሥልጠና | | | |
| . ለቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ረዳቶቻቸው | 50x20x70= 70,000 | - | - |
| . ከኃላፊዎች ጋር ለሚመደቡ ሾፌሮች | 25x20x47= 23,500 | - | - |
| . ከዋናው መ/ቤት የሚመደቡ አሠልጣኞች | 30x14x24= 10,080 | - | - |
| በቅ/ጽ/ቤቶች ለሚሰጥ ሥልጠና | | | |
| . ከዋናው መ/ቤት ለሚመደቡ አሠልጣኞች | 50x22x70= 77,000 | - | - |
| . ከአሠልጣኞች ጋር ለሚመደቡ ሾፌሮች | 25x22x47= 25,850 | - | - |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች | 2166x22x47= 2,239,644 | - | 120x10x47= 56,400 |
| . ለተቆጣጣሪዎች | 406x22x15= 133,980 | - | 120x10x58= 69,600 |
| . ለስታቲስቲሽያኖች | 25x22x24= 13,200 | - | 25x10x70= 17,500 |

## የ1995 የብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የካፒታል በጀት ፍላጎት

| | | | |
|---|---|---|---|
| ለ/ ለሥልጠና II | | | |
| . የትላልቅና የመካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ ጥናት | | . | |
| . የኮንስትራክሽን ጥናት | | | |
| . የአከፋፋይ ንግድና አገ/ ሰጪ ድርጅቶች | | | |
| . የአነስተኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት | | | |
| . መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናት | | | |
| . የዕደ ጥበብና የጎጆ ኢንዱስትሪ ጥናት | | | |
| በዋናው መ/ቤት ለሚሰጥ ሥልጠና | | | |
| . ለቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ረዳቶቻቸው | - | 50x35x70= 122,500 | - |
| . ከቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች ጋር ለሚመጡ ሾፌሮች | - | 25x35x47= 41,125 | - |
| . ከዋናው መ/ቤት ለሚመደቡ አሠልጣኞች | - | 50x20x24= 24,000 | - |
| በቅ/ጽ/ቤት ለሚሰጥ ሥልጠና | | | |
| . ከዋናው መ/ቤት ለሚሠማሩ አሰልጣኞች | - | 50x35x70= 122,500 | - |
| . ከአሠልጣኞች ጋር ለሚመደቡ ሾፌሮች | - | 25x35x47= 41,125 | - |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች | - | 562x35x47= 924,490 | - |
| . ለተቆጣሪዎች | - | 107x20x15= 32,100 | - |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች (ለኢንዱስትሪ ጥናት)* | - | 110x15x18= 29,700 | - |
| . ለቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ረዳቶቻቸው | - | 50x19x70= 66,500 | - |
| . ከቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች ጋር ለሚመጡ ሾፌሮች | | 25x19x47= 22,325 | - |
| ሐ/ ለመስክ ቁጥጥር | | | |
| . ከዋናው መ/ቤት ለሚሰማሩ ባለሙያዎች | 25x90x70= 157,500 | 25x90x70= 157,500 | - |
| . ከባለሙያዎች ጋር ለሚመደቡ ሾፌሮች | 25x90x47= 105,750 | 25x90x47= 105,750 | - |
| . የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ረዳቶቻቸው | 50x90x70= 315,000 | - | - |
| . የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች ጋር ለሚመደቡ ሾፌሮች | 25x90x47= 105,750 | - | - |
| . ለመስክ ተቆጣጣሪዎች | 406x120x58= 2,825,760 | 107x90x58= 558,540 | - |
| . ለመስክ ተቆጣጣሪዎች የበረሃ አበል | 32x120x17.40= 66,816 | - | |
| . ከመስክ ተቆጣጣሪዎች ጋር ለሚመደቡ ሾፌሮች | 150x120x47= 846,000 | 132x90x47= 558,360 | - |
| . ከተቆጣጣሪዎች ጋር ለሚመደቡ ሾፌሮች የበረሃ አበል | 32x120x14.10= 54,144 | - | - |
| . ለኢንዱ.ጥናት መረጃ ሰብሳቢዎች ምሣ አበል | - | 110x90x18= 178,200 | - |
| . ለኢንዱ.ጥናት ተቆጣጣሪዎች ምሣ አበል | - | 33x90x15= 44,500 | - |
| . ከተቆጣጣሪዎች ጋር ለሚመደቡ ሾፌሮች የምሣ አበል | - | 33x90x12= 37,800 | - |
| . የዋጋ ጥናትን መረጃ ወደ 11 ቅ/ጽ/ቤቶች ለማድረስ | - | - | 14x4x58x12= 38,976 |
| . ለሂሣብ ሠራተኞች | 25x90x58= 130,500 | - | - |
| **ንዑስ ድምር** | **7,200,474** | **3,067,015** | **182,476** |

* በትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች እና ለኮንስትራክሽን ጥናት የሚሣተፉ ናቸው::

የቀጠለ

| | | | |
|---|---|---|---|
| VIII የትራንስፖርት ክፍያ | | | |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች በስምሪት ወቅት | 2023x50x1= 101,150 | 562x20x1= 11,240 | - |
| . ለመረጃ ሰብሳቢዎች በሥልጠና ወቅት | 2023x50x2= 202,300 | 562x40x6= 134,880 | 120x50x2= 12,000 |
| . ለተቆጣጣሪዎች በስምሪት ወቅት | 406x50x1= 20,300 | 107x40x6= 25,680 | - |
| . ለተቆጣጣሪዎች የበቅሎ ኪራይ | 406x100x6= 243,600 | - | - |
| . ለዋናው መ/ቤት ኤክስፐርቶች የአየር ትራንስፖርት | 40x600x2= 48,000 | 40x600x2= 48,000 | - |
| . የዋጋ ጥናትን መረጃ ወደ 11 ቅ/ጽ/ቤቶች ለማድረስ | - | - | 14x30x2x12 = 10,080 |
| **ንዑስ ድምር** | **615,350** | **219,800** | **22,080** |
| **IX ለትራንስፖርት ጥገና** | | | |
| . ለተሽከርካሪዎች ጥገና | 251x1000x12= 3,012,000 | - | - |
| . ለተሽከርካሪዎች ጎማ | 251x700x5= 878,500 | - | - |
| **ንዑስ ድምር** | **3,890,500** | - | - |
| **X ለመሣሪያ ጥገና** | | | |
| . ለዋናው መ/ቤት (ለማተሚያና ለኮፒውተር ዕቃዎች) | 100,000 | - | - |
| . ለቅ/ጽ/ቤት | 25x200x12= 60,000 | - | - |
| **ንዑስ ድምር** | **160,000** | - | - |
| **XI ለቢሮና ለሥልጠና አዳራሽ ኪራይ** | | | |
| . ለዋናው መ/ቤት ለስልጠና አዳራሽ ኪራይ | 10,000 | - | - |
| . ለቅ/ጽ/ቤቶች ለ16 ቢሮ ኪራይ | 25,738x12= 308,856 | - | - |
| . ለ3 አዲስ ጽ/ቤቶች ቢሮ ኪራይ | 3x2,000x12= 72,000 | | |
| . ለ25 ቅ/ጽ/ቤቶች የስልጠና አዳራሽ ኪራይ | 25x1000x2= 50,000 | | |
| **ንዑስ ድምር** | **440,856** | | |
| **XII ለኢንሹራንስ** | | | |
| . ለመስክ ሠራተኞች | 3652x143= 522,236 | - | - |
| . ለተሽከርካሪዎች | 251x1980= 496,980 | - | - |
| **ንዑስ ድምር** | **1,019,216** | | |
| **XIII ለኤሌክትሪክ አገ. ክፍያ** | | | |
| . ለቅ/ጽ/ቤቶች | 25x200x12= **60,000** | - | - |

# የ1995 የብሔራዊ የተቀናጀ ስርቬይ ፕሮግራም የካፒታል በጀት ፍላጎት

የቀጠለ

| | | | |
|---|---|---|---|
| XIV ለስልክ አገ. ክፍያ | | | |
| . ለዋናው መ/ቤት ስልክ ፋክስና ኢንተርኔት | 10,000x12= 120,000 | | |
| . ለቅ/ጽ/ቤቶች | 25x800x12= 240,000 | - | - |
| ንዑስ ድምር | **360,000** | | |
| XV ለውሃ፣ ፖስታና ሌሎች አገ.ክፍያ | | | |
| . ለቅ/ጽ/ቤቶች | 25x200x12= 60,000 | - | - |
| . ለዋናው መ/ቤት የባንክ ኮሚሽን | 1500x12= 18,000 | - | - |
| . ለዋናው መ/ቤት ለውኃ ፖስታና ሌሎች አገ. | 1000x12= 12,000 | | |
| ንዑስ ድምር | **90,000** | - | - |
| XVI ለአገር ውስጥ ሥልጠና | **150,000** | | |
| XVII ለቋሚ ዕቃ ግዢ | | | |
| . ኮምፒውተሮችና ፕሪንተሮች | - | 4x22,500= **90,000** | - |
| ድምር | **23,824,938** | **6,600,257** | **932,766** |
| ጠቅላላ ድምር | **31,357,961** | | |

# ለ1995 የአርብቶ አደሩ አካባቢ ግብርና ናሙና ቆጠራ የመረጃ መሰብሰብ ተግባራትን ለማከናወንና በ1994 በአርሶ አደሩ አካባቢዎች በግብርና ናሙና ቆጠራ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለማቀነባበርና የሪፖርት ዝግጅት የቀረበ የካፒታል በጀት ፍላጎት

መንጠረዥ 2

| የወጪ ዓይነት | የአርብቶ አደሩ አካባቢ ግብርና ቆጠራ | የመረጃ ማቀነባበርና ሪፖርት ዝግጅት |
|---|---|---|
| መወዝ | | |
| ረጃ ሰብሳቢ | 1760x381x2= 1,341,120 | |
| ተቆጣጣሪዎች | 320x630x2= 403,200 | - |
| • ለኢዲተሮች | - | 200x530x12= 1,272,000 |
| • ለዳታ ኢንትሪ ኦፕሬተሮች | - | 200x450x12= 1,080,000 |
| • ለሾፌሮች | 46x381x2= 35,052 | - |
| ንዑስ ድምር | 1,779,372 | 2,352,000 |
| II ለሰው ጉልበት ወጪ | | |
| • ለመንገድ መሪና ለአስተርጓሚ | 1600x50x60= 4,800,000 | - |
| • ለቀን ሙያተኛ | - | 20x210x12= 50,400 |
| ንዑስ ድምር | 4,860,000 | 50,400 |
| III ለበረሃና የመጠለያ አበል | | |
| • ለመረጃ ሰብሳቢዎች የበረሃ አበል | 1600x115x2= 368,000 | - |
| • ለተቆጣጣሪዎች " " | 320x189x2= 120,960 | - |
| • ለመረጃ ሰብሳቢዎች የመጠለያ አበል | 1600x30x2= 96,000 | - |
| ንዑስ ድምር | 584,960 | - |
| IV ለአላቂ የቢሮ ዕቃዎች | | |
| • የጽ/መሣሪያ | 24,000 | 80,000 |
| V ለሕትመት | | |
| • ለኬሚካልና ለቀለም | 25,000 | 150,000 |
| VI ለነዳጅና ቅባት | | |
| • ከዋናው መ/ቤት ለሚሰማሩ ባለሙያዎች | 3x20x50x4.30=12,900 | - |
| • ከቅ/ጽ/ቤቶች ለሚሰማሩ ተቆጣጣሪዎች | 19x30x50x4.30=122,550 | - |
| • ለሪፖርት ማስተዋወቅ የሚውል ነዳጅ | - | 10x10x30x4.30=12,900 |
| ንዑስ ድምር | 135,450 | 12,900 |
| VII ውሎ አበል | | |
| ሀ/ ለሥልጠና | | |
| • በዋናው መ/ቤት አሠልጣኞች ሥልጠና | 30x3x25= 2,250 | - |
| • ለመረጃ ሰብሳቢዎች | 1760x7x61.10= 752,752 | - |
| • ለተቆጣጣሪዎች | 320x7x75.40= 168,896 | - |
| • ለአሰልጣኞች | 30x9x91= 24,570 | |
| ለ/ ለመስክ ሥራ | | |
| • ለተቆጣጣሪዎች | 320x30x75.40= 723,840 | - |
| • ከተቆጣጣሪዎች ጋር ለሚመደቡ ሾፌሮች | 46x30x61.10= 84,318 | - |
| • ከዋናው መ/ቤት ለሚመደቡ ባለሙያዎች | 12x20x91= 21,840 | - |
| ሐ/ ሪፖርቶችን ለማስተዋወቅ | - | |
| • ለባለሙያዎች (በማዕከል ደረጃ ለሚሣተፉ) | - | 50x2x25= 2,500 |
| • ለተሣታፊዎች (በማዕከል) | - | 200x2x25=10,000 |
| • ለሾፌሮች (በማዕከል) | - | 10x2x12= 240 |
| • ለባሙያዎች (በክልል ደረጃ ለሚሣተፉ) | - | 16x4x70= 5,600 |
| • ለተሣታፊዎች (በክልል ለሚሣተፉ) | - | 600x4x70=168,000 |
| • ለሾፌሮች (ከባለሙያዎች ጋር ለሚሣተፉ) | - | 8x5x47= 1,880 |
| ንዑስ ድምር | 1,778,466 | 188,220 |

## ለ1995 የአርብቶ አደሩ አካባቢ ግብርና ናሙና ቆጠራ የመረጃ መሰብሰብ ተግባራትን ለማከናወንና በ1994 በአርሶ አደሩ አካባቢዎች በግብርና ናሙና ቆጠራ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለማቀነባበርና የሪፖርት ዝግጅት የቀረበ የካፒታል በጀት ፍላጎት

የቀጠለ

| የወጪ ዓይነት | የአርብቶ አደሩ አካባቢ ግብርና ቆጠራ | የመረጃ ማቀነባበርና ሪፖርት ዝግጅት |
|---|---|---|
| VIII. የትራንስፖርት ወጪ | | |
| • ለመረጃ ሰብሳቢዎች | 1760x100x2= 352,000 | |
| • ለተቆጣጣሪዎች (የግመል ኪራይ) | 320x20x50= 320,000 | 8x400x2= 6,400 |
| • ለባለሙያዎች (ለአይሮፕላን ጉዞ) | 4x400x2= 3,200 | 400x50x2= 40,000 |
| • ሪፖርት ቅውውቅ ላይ ከክልል ለሚሣተፉ | | |
| **ንዑስ ድምር** | **675,200** | **46,400** |
| XI. ለመስተንግዶ | | |
| • ለማዕከል ሴሚናር ተካፋዮች | 260x30x2x2ጊዜ=31,200 | 260x30x2x2ጊዜ=31,200 |
| • ለክልል ሴሚናር ተካፋዮች | 100x30x2x2ጊዜ=12,000 | 630x30x2x2ጊዜ=75,600 |
| **ንዑስ ድምር** | **43,200** | **106,800** |
| X ለትራንስፖርት ጥገና | | |
| • ለተሽከርካሪዎች ጥገና | 46x1000x3= 138,000 | - |
| • ለተሽከርካሪዎች ጎማ | 46x700x5= 161,000 | - |
| **ንዑስ ድምር** | **299,000** | - |
| XI ለማስታወቂያ አገልግሎት | | |
| • ለተለያዩ ፖስተሮችና በራሪ ወረቀቶች | - | 200,000 |
| • ለትምህርትና ቅስቀሳ ተግባር | 50,000 | - |
| **ንዑስ ድምር** | **50,000** | **200,000** |
| XII ለኢንሹራንስ | | |
| • ለመስክ ሠራተኞች | 2010x143x2= 574,860 | - |
| • ለተሽከርካሪዎች | 46x1980x2= 182,160 | - |
| **ንዑስ ድምር** | **757,020** | |
| **ድምር** | **10,951,668** | **3,186,720** |
| **ጠቅላላ ድምር** | **14,138,388** | |

## 7. የ1995 ጥናቶች ግብና መግለጫ

### 7.1 የ1995 ጥናቶች ግብ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1995 በጀት ዓመት በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ሥር አስራ ሁለት የተለያዩ ጥናቶችን በአገሪቱ ገጠርና ከተማ በናሙና በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች ላይ ለማካሄድ አቅዷል:: እንደዚሁም በ1994 ዓ.ም መካሄድ የነበረበት የአርብቶ አደሩ የግብርና ናሙና ቆጠራ በዓመቱ አመቺ ጊዜ ባለመገኘቱ የተነሳ በ1995 ዓ.ም ሊካሄድ በመታቀዱና በአርሶ አደሩ አካባቢ በ1994 በተካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ ሂደት የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለማቀነባበርና የሪፖርት ዝግጅትም ለማከናወን አቅዷል::

በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም አማካይነት የሰው ኃይል፣ ሎጂስቲክስና በጀትን በማቀናጀት ከሚካሄዱት ጥናቶች መሐል ከዋጋ ጥናት በስተቀር ሁሉም በተያዘላቸው መርሃ ግብር መሰረት የሚጠናቀቁ ሲሆኑ፣ የዋጋ ጥናትን በተመለከተ ግን ጥናቱ የሚጀመረው በሐምሌ ወር ቢሆንም የማይቋረጥና በየወሩ የሚከናወን በመሆኑ የቅንብሩ ሥራ የመጨረሻዎቹን ሁለት ወራት መረጃ በቀጣዩ በጀት ዓመት የሚከናወን ይሆናል:: በ1994 ዓ.ም አርሶ አደሩ አካባቢ በተካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ የተሰበሰቡ መረጃዎችን የመረጃ ማቀነባበርና የሪፖርት ዝግጅትን በተመለከተ በዚህ በጀት ዓመት የሚከናወነው ተግባር የተሰበሰቡ መረጃዎችን የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግ፣ የዳታ ኢንትሪ እንዲሁም መረጃዎቹን የማቀነባበር፣ የመገምገምና ሪፖርት የማዘጋጀት ተግባርና እንደተያዘላቸው ቅደም ተከተል ሪፖርቶችን የማተምና የሚመለከታቸው የሪፖርት ተጠቃሚዎች የማስራጨትና የማስተዋወቅ ሥራ /Dessimination Seminar/ ማካሄድ ይሆናል::

### 7.2 የ1995 ጥናቶች ዝርዝር መግለጫ

#### 7.2.1 የአምራቾች የዋጋ ጥናት ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

በየወሩ የግብርና ውጤቶች የአምራች ዋጋ ጥናት በገጠር በተመረጡ 446 የቆጠራ ቦታዎች ይካሄዳል:: ከዚህ ጥናትም በሚሰበሰቡ መረጃዎች በየወሩ በአገር አቀፍ፣ በክልልና በዞን ደረጃ በሪፖርት መልክ ይወጣሉ::

ሀ. የአምራቾች ዋጋ ጥናት ዓላማዎች

የአምራቾች ዋጋ ጥናት በገጠር በየወሩ የሚሰበሰብ ሲሆን የጥናቱ አበይት ዓላማዎች፣

- ፖሊሲ አውጪዎች ስለእርሻ ውጤቶች ምርትና ሥርጭት አስመልክቶ ውሳኔ ለመስጠት የሚረዱ መረጃዎች፣

- ገበሬዎች በአምራቾች ደረጃ ለእርሻ ውጤቶች የሚያስከፍሉትን ዋጋ መጠን ለማጥናት መሠረት የሆኑ መረጃዎች፣
- የምርት ጠቅላላ ዋጋና የሀገር ሀብት ውጤትን ለማስላት የሚረዱ እንደዚሁም በኢኮኖሚው ላይ የሚታየውን ለውጥ ለማጥናት መነሻ የሚሆኑ መረጃዎች፣
- የእርሻ ውጤቶችን በሚመለከት የአምራች ዋጋን የምርት መጠን መመዘኛ ኢንዴክሶችን ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ መረጃዎች መሰብሰብ ናቸው።

ለ. <u>በአምራቾች ዋጋ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

ለአምራቾች ዋጋ ጥናት በገጠር በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች የግብርና ውጤቶች የአምራች ዋጋ መረጃ የሚሰበሰብ ሲሆን እነዚህም የእህል፣ የጥራጥሬ፣ የቅባት እህሎች፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የቅመማቅመም፣ የወተትና የወተት ተዋፅኦ፣ እንቁላል፣ የቁም ከብቶች፣... ወዘተ የዋጋ መረጃዎች ይሰበሰባሉ።

7.2.2 <u>የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት፣</u>

ሀ. <u>የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ዓላማዎች</u>

የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በከተማ የሚገኙ 120 ትላልቅ ገበያዎች የሚሰበሰብ ሲሆን የጥናቱ ዋና ዓላማዎች:-

- የችርቻሮ ዋጋ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ማወቅ፣
- በተለያዩ የሥርጭት ደረጃዎች መካከል ያሉትን የዋጋ ልዩነቶች ለማወቅ፣
- በኢኮኖሚው ላይ የሚታየውን ለውጥ ለመገምገም፣
- ለቤተሰብ ፍጆታ የዋሉትን ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋ ለመተመን፣
- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ምርትና ስርጭት በሚመለከት ፓሊሲ አውጪዎች ውሳኔ ለመድረስ የሚያስችሉ መነሻ መረጃዎች ለማግኘት፣
- የምርትን ጠቅላላ ዋጋና የሀገር ሀብት ውጤትን ለማስላት እንደዚሁም የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ለማዘጋጀት የሚያስችሉ መረጃዎች መሰብሰብ ናቸው።

ለ. በችርቻሮ ዋጋ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት፡-

ለችርቻሮ ዋጋ ጥናት በከተማ ከተመረጡ ትላልቅ ገበያዎች / በዋና ዋና የመገበያያ ሥፍራዎች /የእርሻና የኢንዱስትሪ ውጤቶች ከግል ነጋዴዎች የችርቻሮ ዋጋ መረጃ የሚሰበሰብ ሲሆን እነዚህም የምግብ፣ የመጠጥ፣ የትምባሆ፣ የልብስ፣ የጫማ፣ የሕንፃ መሣሪዎች፣ የቤት ኪራይ፣ የቤት መገልገያ ዕቃዎች፣ የሕክምና መድኃኒት፣ የመጓጓዣ፣ የትምህርት፣ የመዝናኛ፣ የእርሻ መገልገያ መሣሪያዎች፣ የሆቴል ምግብና አልጋ... ወዘተ የዋጋ መረጃዎች ናቸው::

7.2.3 የተፈበረኩ ዕቃዎች የአምራቾች ዋጋ የሙከራ ጥናት/ በከተማ/

ሀ. የተፈበረኩ ዕቃዎች የአምራቾች ዋጋ ጥናት ዓላማዎች

ጥናቱ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች በሙሉ /ትላልቅና መካከለኛ/ የሚሰበሰብ ሲሆን፣ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

- ፖሊሲ አውጪዎች ስለኢንዱስትሪ ውጤቶች ምርትና ስርጭት ለሚወስዱት ውሣኔ እንዲረዳ፣
- ባለፋብሪካዎች በአምራች ደረጃ ለኢንዱስትሪ ውጤቶች የሚያስከፍሉትን የዋጋ መጠን ለማጥናት፣
- የምርትን ጠቅላላ ዋጋና የሃብት ውጤትን ለማስላት የሚረዱ እንደዚሁም በኢኮኖሚው ላይ የሚታየውን ለውጥ ለማጥናት መነሻ የሚሆን መረጃ ለማግኘት፣
- በተለያዩ የስርጭት ደረጃዎች ያሉትን የዋጋ ልዩነቶች ለማጥናት፣
- የኢንዱስትሪ ውጤቶችን በሚመለከት የአምራች ዋጋ ኢንዴክሶችን ለማዘጋጀት እንዲያገለግል ነው::

ለ. የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት

- የአምራቾች ሙሉ አድራሻ በየከተማው፣
- ምርታቸው የሚሸጡበት አድራሻ፣
- የዕቃዎች ዓይነት መለየት (Item Sepcification) እና፣
- የዕቃዎች ዋጋ ናቸው::

7.2.4 <u>የጅምላ ዋጋ ጥናት /በከተማ/</u>

ሀ. <u>የጅምላ ዋጋ ጥናት ዓላማዎች</u>

ጥናቱ በናሙና ከሚመረጡ የግብርና የኢንዱስትሪ ውጤት ጅምላ ነጋዴዎች የሚሰበሰብ ሲሆን ፣ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

- ፖሊሲ አውጪዎች በአገሪቱ ስላለውና ስለሚኖረው የጅምላ ንግድ ለሚወስዱት ውሣኔ እንዲረዳ፣
- የጅምላ ነጋዴዎች ለዕቃዎች የሚያስከፍሉትን ዋጋዎች ለማጥናት፣
- በተለያዩ የስርጭት ደረጃዎች ያሉትን የዋጋ ልዩነቶች ለማጥናት፣
- በኢኮኖሚ ላይ የሚታየውን ለውጥ ለማጥናት፣ እና
- የጅምላ ዋጋ ኢንዴክስ ለማስላትና ለማዘጋጀት እንዲያገለግል ነው።

ለ. <u>የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

- የጅምላ ነጋዴዎች አድራሻ፣
- የሚነግዱቸው ዕቃዎች ዓይነት (Item Specification)
- የዕቃዎቹ ዋጋ... ወዘተ ናቸው።

7.2.5 <u>የትላልቅና መካከለኛ የማመረቻ ኢንዱስትሪዎት ጥናት ዓላማዎችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

በዚህ ጥናት አሥርና ከአሥር በላይ ሠራተኞች ከሚያሰማሩ፣ በአንድ ሥፍራ የተለየ አድራሻ ካላቸው፣ አብዛኛው ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ ሆኖ በኢነርጂ ወይም በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ መሣሪያ በመጠቀም አንድ ወይም የተለያዩ ምርቶችን ከሚያመርቱ ፋብሪካዎች ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የሚሰበሰቡ ሲሆን ጥናቱ የሚካሄደውም በከተማዎች ክልል ነው።

ሀ. <u>የትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ዓላሚ</u>

የትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት አበይት አላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

- የዘርፉን ዕድገት በሚመለከት የኢኮኖሚ ፓሊሲና የልማት ዕቅድ አውጪዎች እንደዚሁም ተመራማሪዎች በመነሻነት የሚጠቀሙበት ስታቲስቲካዊ መረጃ በኢንዱስትሪና በባለቤትነት ዓይነት ለማቅረብ፣

- ዘርፉ ያስማራውን የሰው ኃይልና የምርት መጠን ለማወቅና ለሀገር ሀብት ውጤት የሚያበረክተውን ድርሻ ለማስላት አስፈላጊ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለማግኘት፣

- ዘርፉ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች በተለይም ከግብርናው ጋር ያለውን መስተጋብር እንዲሁም ከውጭ ጥሬ ዕቃዎችን በማስገባት በኩል ያለውን ድርሻ ለመገመት የሚያስችሉ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በዝርዝር መሰብሰብ ናቸው።

ለ. <u>የትላልቅና መካከለኛ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናትና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

- የፋብሪካው ሕጋዊ አቋም፣
- የተከፈለ ካፒታል መጠን ( Paid -up Capital)፣
- የሠራተኞች ብዛት፣ ደመወዝና ምንዳ፣
- የምርት መጠንና ዋጋ፣
- የጥሬ ዕቃ ፍጆታ፣
- ልዩ ከማምረት ይዘት ጋር የተዛመዱና ያልተዛመዱ ወጪዎች፣
- የቋሚ ንብረት ዓይነትና በቋሚ ንብረት ላይ የተደረገ የመዋዕለ ንዋይ መጠን፣
- የማምረት ችሎታ፣ ... ወዘተ አመልካች መረጃዎችን ይሰበሰባሉ።

7.2.6 <u>የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት (በከተማና በገጠር)</u>

የዚህ ጥናት አላማ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ለሀገር ሀብት ውጤት (GDP) የሚኖራቸውን አስተዋጽኦ /ድርሻ/ ለማስላትና በዚህ የኢኮኖሚ ዘርፍ ያሉት ድርጅቶችን የዕድገት አቅጣጫ ለመገምገምና እንደዚሁም ለሚዘጋጁ ዕቅዶች አፈጻጸምና ክትትል የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ሰብስቦና አቀነባብሮ ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ ነው።

ለዚህ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነትም:-

- የድርጅቶች ብዛት፣
- የተከፈለ ካፒታል መጠን በይዞታ፣

- ሕጋዊ አቋም፣
- የሠራተኞች ብዛትና የተከፈለ ደመወዝ መጠኝ፣
- የምርትና የሽያጭ መጠንና ዋጋ፣
- የጥሬ ዕቃዎች ፍጆታ መጠንና ዋጋ፣
- ልዩ ልዩ ገቢዎችና ወጪዎች፣ እና
- የቋሚ ንብረትና የመዋዕለ ንዋይ ወጪ ናቸው::

7.2.7 የጎጆና የዕደ-ጥበብ ኢንዱስትሪዎች ጥናት (በገጠርና በከተማ)

የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ የዚህ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሀገር ሀብት ውጤት (GDP) የሚያበረክቱትን ድርሻ ለማስላትና የዘርፉን የእድገት አቅጣጫ በመገምገም ለዕቅድ ዝግጅት ለክትትልና ለምርምር የሚያገለግሉ መሠረታዊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው::

በጥናቱ የሚሰበሰቡ ዋና ዋና መረጃዎችም:-

- የጎጆና የዕደ-ጥበብ ኢንዱስትሪዎች ብዛት፣
- የባለቤትነት ዓይነትና ሕጋዊ አቋም፣
- የሠራተኞች ብዛትና የተከፈለ ደመወዝ መጠኝ፣
- የምርምርና የሽያጭ መጠንና ዋጋ፣
- የጥሬ ዕቃዎች ፍጆታ መጠንና ዋጋ፣
- ልዩ ልዩ ወጪዎችና ገቢዎች ናቸው::

7.2.8 የኮንስትራክሽን ጥናት

ሀ. የኮንስትራክሽን ጥናት ዓላማዎች

የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ጠቋሚ የሆነው የኮንስትራክሽን ዘርፍ ጥናት የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት::

- የዘርፉን ዕድገት በሚመለከት የኢኮኖሚ ፖሊሲና የልማት ዕቅድ አውጭዎች እንደዚሁም ተመራማሪዎች በመነሻነት የሚጠቀሙበት ስታቲስቲካዊ መረጃዎች በባለቤትነት ዓይነት ለማቅረብ፣

- ዘርፉ ያሰማራውን የሰው ኃይል እንደዚሁም ለአገር ሀብት ውጤት የሚያበረክተውን ድርሻ ለማስላት የሚያስችል ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለማግኘት፣

- ዘርፉ የሌሎች የኢኮኖሚና የማህበራዊ ዘርፎች እንቅስቃሴ በማገዝ በኩል ያበረከተውን ድርሻ ለመገመት የሚያስችል ዝርዝር ስታቲስቲካዊ መረጃ ለማግኘት የሚሉ ናቸው።

ለ. <u>በኮንስትራክሽን ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት</u>

በጥናቱ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት የሚከተሉት ናቸው፣ እነዚህም

- የባለቤትነት ዓይነት፣
- የተከፈለ ካፒታል (Paid-up Capital) መጠን፣
- በሥራው የተሰማራው የሰውኃይል ብዛት፣ ደመወዝና ምንዳ፣
- የኮንስትራክሽን ዓይነትና ውጤት መጠን፣
- ጥቅም ላይ የዋለ የኮንስትራክሽን ጥሬ ዕቃዎች ዓይነትና ሌሎችም ወጪዎች... ወዘተ ናቸው።

